https://chilot.me

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ/መ/ቁ/ 220195

የካቲት 25 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካቾች፡-

1. ዶ/ር አወቀ አጥናፉ አዳም
2. ወ/ሮ ሶፊያ አልማዉ ባቡክር
3. ሙሃጂብ አ ብዱ ኪመቶ
4. ፋንታዬ ባበቡሉ ባጋሮ
5. አቶ ገብሩ አለባቸዉ አዉደዉ
6. አቶ አድነዉ ተስፋዬ አሊ
7. ወ/ሮ ማርታረጂምዳኪማልቲ
8. አቶ አለበል አመራ ታምራት
9. አቶ ጁነይዲ ኢስማን ኢሳ
10. አቶ አበራ ቀዲዳ ቴሶ
11. ወ/ሮ አማረች ባሰዉ ማለዳ
12. አቶ ግዛ ዮሀንስ አሊቶ
13. አቶ ባዘዘዉ ተሰራ ገዳሙ
14. አቶ አለባቸዉ ላቀዉ ሃጂ
15. አቶ ነጋልኝ ዮሴፍ እጉ
16. አቶ አለሙ ይመር ጌታሁን
17. አቶ አበበ አረጋ አየለ
18. እባቡ ብርሌ አየለ

19. አቶ አበበ ጎዴቦ ሽመሎ
20. አቶ አሰፋ ረሺድ ከማል
21. ወ/ሮ ትእግስት አለማየሁ በጅጋ
22. አቶ ታደሰ ሆርዶፋ አያኔ
23. አቶ ጀምበር አስማመዉ በላይ
24. አቶ ሙስጠፋ ወርቁ ጥቻ
25. አቶ ተመስገን ጎዳና ጂቦ
26. አቶ መስፍን መሸሻ የቦ
27. አቶ ወንደሰን ወጋየሁ ደስታ
28. አቶ ናስር ካንሶ ካይጸ
29. አቶ ሽመልስ አበባዉ ሽፈራዉ
30. አቶ ፉፊ ድልጋሳ ዳዬ
31. አቶ ጌታቸዉ መለሰ በላይ
32. ወ/ሮ ሃላኩ ጎዳና ኩና
33. ወ/ሮ ሪሃና መሀመድ ይመር
34. ወ/ሮ ሙሉነሽ መኮንን በላይ
35. ኑሪያ ባሙድ ሁሴን
36. የወ/ሮ ሙንታሓ ኢብራሂም አህመድ
37. አቶ አመልመሃመድአደም
38. አቶ ተመስገን በቀለ ጌቾ
39. ወ/ሮ እጥፍ ወርቅ ዘዉዱ እንድሪስ
40. ወ/ሮ ተዋበች አሰፋ ሳፎ
41. አቶ ታደለ ዘዉዴ አበበ
42. አቶ ታከለ ወ/ገብርኤልብሩ
43. አቶ ተሸመ እሸቱ በለጠ
44. አቶ አክሊሉ ጌታቸዉ ናዴ
45. ወ/ሮ መስከርም ወርቁ ነሜ
46. አቶ ዋቅጅራ ተርፋሳ ከበደ
47. አቶ ብርሀኑ አበበ ደገፋ
48. አቶ ጀማልኢመርመንዛ
49. አበባዉ በቀለ አንድሬ
50. ወ/ሮ ሃምዚያ ጀማል ሁሴን
51. አቶ ኑርአሚን ሰይድ አብዱልሰላም
52. ወ/ሮ ባንቹ ሙሉጌታ መሪ
53. ወ/ሮ ፌይሴ ለሜሳ ጌማ
54. አቶ አለሙ አሰፋ አበበ
55. ወ/ሮ ቡልቱ ሊካሳ ተርፋ
56. ወ/ሮ አገሬ ማናለ ገዳሙ
57. አቶ መልካሙ ስሬ ካሳ
58. አቶ አባይነ ተላከ ላየዉ
59. ወ/ሮ ፋንታዬ ወንድሙ ላቀዉ
60. አቶ ወንድሙ ገላጋይ ተሻለ
61. ወ/ሮ አሪሚና እንዲሪስ አዳም
62. አቶ አብዶ ናስር ሃጂ መሐመድ
63. ወ/ሮ አልማዝ መኮንን ወንድም ገዛው
64. ወ/ሮ ዱሌ ተሰማ ጃዎ
65. ወ/ሮ ጀንበርነሽ ክንፈ ሐይሌ
66. በላይነሽ ታደሠ ዋቂ
67. ወ/ሮ ፅጌ መቆያ ተ/ስላሴ
68. ወ/ሮ ሽምሺ ቃሲም ወዳይ
69. ወ/ሮ ታደለች ከበደ ሐብቴ
70. ወ/ሮ የወይንሃረግ ደምሴ ቱሉ
71. ወ/ሮ ዘይነባ ናስር ሰይድ
72. ወ/ሮ ሽብሬ ሽሪፈ አባጎጃም
73. ወ/ሮ ነሂማ አህመድ ዩሱሰፍ
74. አቶ ሞገስ ታደሰ አለሙ

75. ወ/ሮ ውድነሽ ክፍሌ ደገፋ
76. አቶ ሺኩሪ መዓሊን ሁሴን
77. አቶ አቡ ብርኪ ቱኬ
78. አብድላ ሐሙ ግንቢቴ
79. ጥሩነሽ ጣሪቅ
80. አረጋ ፋፋ
81. ኤሌማ ቃምፔ
82. ሠናይት አንዳርገ
83. ስመኝ ገ/ህይወት
84. ቦኒያኡዴሳ
85. ወ/ሮ ወርቅነሽ ታደሰ እንዳለው
86. አቶ ታዛቢ በየነ ጎላ
87. ወ/ሮ ወይኒቱ መልኩ በለጠ
88. አቶ ሂብራሂም ሰዲቅ መሐመድ
89. አቶ አሊ ኡስማን ቱርኪ
90. አቶ አሊ መሐመድ አህመድ
91፡. ዶ/ር ጥለሁን አየለ ደኑ
92. አቶ ሰይድ ጫላ ዳቃ
93. አቶ ደርጊሶ ጎና ጎሎ
94. ወ/ሮ አባይነሽ ሸካ ሙንዳ
95. ወ/ሮ ሪቢያ ኢሳ ቢነግዴ
96. አቶ ጉልላት ድብሬ ደሜ
97. ወ/ሮ ይታይሽ አበጀ ገላዬ
98. ወ/ሮ እምዬ ቢተው ደስታ
99. ወ/ሮ እፀገነት ምህረት በየነ
100. አቶ ፀጋዬ አህመድ ሰይድ
101. አቶ ዘላለም ታረቀኝ ጥሩነህ
102. ወ/ሮ እቴነሽ ዘለለ ሰቦኖ
103. አቶ ታምሬ ድቱሶ ወተሌ
104. ወ/ሮ አልማዝ መሰለ ማሳ
105. ወ/ሮ ገነት አባታ ገላልቻ
106. አቶ አብዱላሂ እስማኤል ጎበና
107. አቶ አንዳርጌ በላይ ተሰማ
108. አቶ ሙህዲን አባሞጋ አባገሮ
109. አቶ አያሱ ወርቅነህ ታረቀ
110. አቶ ፍርዱ አየለ መስፍን
111. አቶ ዮሴፍ ዳእሞ አበበ
112. አቶ አዲስ ከበደ እንግዳ
113. ወ/ሮ አበባዬ ገዛኸኝ ፈየራ
114. አቶ በድሩ መሐመድ ኑሩ አባፎጊ
115. ወ/ሮ ፈትህ ዮሴፍ መሐመድ
116. አቶ ታሪኩ ደምሴ ጉዬ
117. ወ/ሮ ገነት አብደላ መሐመድ
118. ወ/ሮ ኢፍቱ ቶፊቅ አብደላ
119. ወ/ሮ ቸርነት ኃ/ማርያም ጉደታ
120. ወ/ሮ የውብዳር አሚኖ ቶሬቤላ
121. አቶ ሰይድ አባቦር አባዋጅ
122. አቶ ሚናስ እሩይ ስላይኑ
123. አቶ ቡንቱቃ ዋሬ ጃሌ
124. ወ/ሮ አንጓች ደሳለኝ ብሩ
125. ወ/ሮ ካሰች አዲስ መንግስቱ
126. ወ/ሮ ሣራ አቤ ዳምጠው
127. አቶ ገረመው ኡጋ መርጋ
128. ወ/ሮ ትግስት ባያኖ ኮምኬስ
129. አቶ ወንዱአለ ባሰው ካሣሁን
130. አቶ ጉህሽ አምባዬ ገ/ማርያም

131. ወ/ሮ አስካለ ጥላሁን ተሰማ
132. አቶ ድልነሳ አንድዓለም አሸናፊ
134. አቶ ንብረት ፋንታሁን ምስክር
133. አቶ ከበደ ዘገየ ታከለ
135. ወ/ሮ መሠረት መንግስቱ ጌታሁን
136. አቶ አሰፋ ጫቅሌ አየለ
137. አቶ ሰንደቅ እጅጉ አሳየኸኝ
138. ወ/ሮ ወርቅነሽ ዮሐንስ ባልቻ
139. አቶ አትክልት ዓለሙ በለው
140. ወ/ሮ ገነት በየነ ሁንዴ
141. ወ/ሮ አፀደ ከበደ አለሙ
142. ወ/ሮ ሰነ ፀሐይ ብዙነህ ከበደ
143. አቶ ገበያዉ አለሙ ምህረቴ
144. ወ/ሮ ካስወይ መስፍን ገ/ህይዋት
145. አቶ ዘለቀ መሀሪ ቢተወልኝ
146. ወ/ሮ ተዋበች ላንቃሞ ላታሞ
147. አቶ ተስፋዬ ጌትነት አመራ
148 አቶ አባድር ፋርስ ሙለታ
149. አቶ ደጀኔ እሸቱ ወርቁ
150. ወ/ሮ ንፁህ አለም ሽፈራው
151. አቶ ትርፌሳ ሰፋ ተስገራ
152. አቶ ሎሰማን አሊ ማሳ
153. ወ/ሮ ነሂማ ታጅ አባመጫ
154. ወ/ሮ ዘውዲቱ ቶንጃ አዳሬ
155. አቶ ልጅአለም ወልዴ ማለፊያ
156. ወ/ሮ ፊጡማ የሱፍ አህመድ
157. ወ/ሮ ውድነሽ ሃይማኖት ተስፋዬ
158. ወ/ሮ መስከረም ማልጌ ማዳ
159. አቶ አብዲ ሙሴ አርቴ
160. ወ//ሮ ሙሚና መሐመድ አህመድ
161. ወ/ሮ ሃዋ አቢመጫ አባፊጣ
162. ዳ/ር ኮረፋ ጋሪኔ አህመድ
163. አቶ ሹክሪ መአሲን

https://chilot.me

ተጠሪዎች፡ 1. የኢ.ፌ.ድ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

2. የኢ.ፌ.ድ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካቾች ጥር 24 ቀን 2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 203460 እና በተጣመረው መ.ቁ. 203280 ታህሳስ 05 ቀን 2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 33(2) መሰረት ያቀረቡትን ክስ ውድቅ በማድረግ የሰጠውን ብይን በማጽናት፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 282281 ጥር 23 ቀን 2014 ዓ.ም የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ ሁከት ይወገድ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር የአሁን አመልካቾች ከሳሾች፤ የአሁን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁን አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት በአጭሩ፡- አመልካቾች በምርጫ ሁለት ጊዜ እና ከዚያ በላይ አገልግለናል፤ ከኃላፊነት ለተነሱ የሀገር እና የመንግስት መሪዎች፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች፣ የምክር ቤት አባላት መብት እና ጥቅማጥቅም የተደነገገውን መብታችን ሳያከብሩ ከያዝነው ቤት በአስቸኳይ እንዲለቁ የተባሉ መሆኑን በመግለጽ መኖሪያ ቤት ሳይሰጠን ከሚኖርበት ቤት እንዳይወጡ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን 2ኛ ተጠሪ ለቀረበው ክስ የሰጠው መልስ አመልካቾች ለተተኪ አዲስ የምክር ቤት አባላት መተላፍለ ያለበት ቤት ላይ ኪራይ እየከፈልን እንቀጥላለን እንጂ አንለቅም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር የምክር ቤት አባላትን ጥቅማጥቅም ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 40/2012 የሚቃረን ነው፤ በአዋጅ ቁጥር 653/2001 እና በተሸሻለው አዋጅ ቁጥር 1003/2009 እንዲሁም በመመሪያ ቁጥር 40/2012 መሰረት ለተሰናባች የምክር ቤት አባላት የኪራይ ቤት የማመቻቸት ኃላፊነት

https://chilot.me

ከሶስቱ የመንግስት አካላት አንዱ የሆነው የአስፈጻሚው አካል ተግባር እንጂ የህግ አውጪው ምክር ቤት እና ጽ/ቤቱ አይደለም፤ አመልካቾች አንወጣም ብለው የያዟቸው ቤቶች የምክር ቤት ጽ/ቤት ከ1ኛ ዙር ጀምሮ በየዙሩ ለሚመጡ የምክር ቤት አባላት እንዲኖሩበት እየደለደለ የሚያስተዳድራቸው ቤቶች በመሆናቸው የምርጫ ዘመናቸው ተጠናቆ ከተሰናበቱ በኋላ ቤቶቹ ውስጥ የሚኖሩበት ምንም ህጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመግለጽ የአመልካቾች ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 33(2)፣(3) እና 244(2) መሰረት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ክስ ለመስማት በተያዘው ቀን ቀጠሮ ባለመቅረቡ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 70(ሀ) መሰረት ጉዳዩ በሌለበት ታይቷል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም በመቃወሚዎች ላይ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካቾች ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም አላቸው ወይስ የላቸውም የሚለውን ጭብጥ ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር ከመረመረ በኋላ በአዋጅ ቁጥር 906/2007 አንቀጽ 5(7) መሰረት ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ቤቶች የሚያስተዳድረው 2ኛ ተጠሪ ሆኖ ሳለ አመልካቾች ከቤቶቹ ጋር በተያያዘ 1ኛ ተጠሪን ሊጠይቁም ሆነ ሊፈጸም የሚችል መብት እና ጥቅም የላቸውም፤ ለክርክር መነሻ የሆኑት ቤቶች አመልካቾች የምክር ቤት አባላት ሆነው ተመርጠው ሲገቡ 2ኛ ተጠሪ ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ተከራይቶ ለመኖሪያ ቤት እንደሰጣቸው በግራ ቀኙ ታምኗል፤ አመልካቾች አሁን የምክር ቤቱ አባላት ሳይሆኑ ተሰናባች የቀድሞ የምክር ቤት አባላት በመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 906/2007 ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም፤ አመልካቾች በአዋጅ ቁጥር 1003/2009 የተሰጣቸውን መብት እና ጥቅማጥቅም የሚመለከተውን አካል ሊጠይቁ ከሚችሉ በቀር ከ2ኛ ተጠሪ ሊጠይቁ የሚችሉበት የሕግ አግባብ የለም፤ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ቤቶች ያገኟቸው የምክር ቤት አባል ሆነው በስራ ላይ እያሉ እንዲገለገሉበት እና ድጋሚ ካልተመረጡ በመመሪያ ቁጥር 40/2012 መሰረት የመመለስ ግዴታ አለባቸው፤ ስለሆነም አመልካቾች በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ላይ ክስ ለማቅረብ መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 33(2) መሰረት ያቀረቡትን ክስ በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የስር ፍ/ቤት ብይን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካቾች ይህን ውሳኔ በመቃወም ጥር 24 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም፡- 2ኛ ተጠሪ አመልካቾች አሁን ላይ የምንኖርባቸውን ቤቶች እንድንለቅ መጠየቁን እና ሁከት ስለመፍጠሩ ማስረጃ አቅርበናል፤ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን መያዝ የለባቸውም ቢል እንኳን ተገቢውን ማስረጃ አቅርቦ በፍሬ ነገር ክርክር ወቅት ተከራክሮ ነፃ ሊወጣ የሚችልበት እንጂ ገና ከመጀመሪያው አይመለከተውም ተብሎ መዝገቡ የተዘጋበት አግባብ የሕግ ድጋፍ የለውም፤

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://chilot.me

አመልካቾች ሲያገለግሉ የቆዩት በተጠሪዎች ስር እስከነበረ ድረስ የእነሱን ጥቅም በተመለከተ ከሦስቱ የመንስግስት አካላት ውስጥ በዋነኝነት እና በቀጥታ ተጠሪዎችን አይመለከትም ተብሎ አይገመትም፤ የሥር ፌርድ ቤት አመልካቾች ቤቱን ለቀን እንድናስረክብ በማለት የሰጠው ብይን የአዋጅ ቁጥር 653/2001ን አላማ ያላገናዘበ ነው፤ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ብይን እና ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ ከመረመረ በኋላ የአሁን የሰበር አመልካቾች ተጠሪዎችን የመክሰስ መብት እና ጥቅም የላችሁም ተብሎ በሥር ፍርድ ቤት የተሰጠው ብይን 2ኛው ተጠሪ ቤቱን ልቀቁ ብሎ ማስገደዱ ያልተከደ ከመሆኑ አኳያ እና በአዋጅ ቁጥር 653/2001 እና አዋጅ ቁጥር 1003/2009 አንቀጽ 15(3)፣ 15(4)(ለ) እና 27(7)(ሀ) ድንጋጌዎች ለሰበር አመልካቾች ከተሰጠው መብት አንፃር አግባብነቱን ለማጣራት ሲባል ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

1ኛ ተጠሪ የፍርድ ቤቱ መጥሪያ ደርሶት መልሳቸውን በቀጠሮ ቀን ያላቀረቡ ስለሆነ መልስ በጽሁፍ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

2ኛ ተጠሪ የካቲት 03 ቀን 2014 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- አመልካቾች ክርክር ወደ አስነሳው ቤቶች ገብተው ለመኖር የቻሉት የህዝብ ተመራጭ በመሆናቸው ነው፤ ተጠሪም ቤቶቹን ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን የተከራያቸው መሆኑ አልተካደም፤ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአባላትን ጥቅማ ጥቅም ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 40/2012 አንቀጽ 11(10)( ሀ) መሰረት የውክልና ጊዜያቸው በማብቃቱ ቤቶቹን ለቀው ሊወጡ ይገባል፤ 2ኛ ተጠሪ ቤቶቹን እንደሚያስተዳደር በአዋጅ ስልጣን የተሰጠው ሲሆን አመልካቾች የውክልና ጊዜያቸውን ሲጨርሱ ቤቶቹን እንዲለቁ መጠየቁ የሁከት ተግባር ካለመሆኑም ባሻገር አመልካቾች በቤቱ ውስጥ ከነሐሴ 30 በኋላ ለመኖር የሚያስችላቸው ህጋዊ መብት አላረጋገጡም፤ በአዋጅ ቁጥር 653/2001 እና 1003/2009 መሰረት የ40/60 መኖሪያ ቤቶች እንደተሰጣቸው አልተካደም፤ የተሰጣቸውን የ40/60 ቤቶችን አለመጠናቀቅ ምክንያት በማድረግ አሁን የሚኖሩበትን ቤቶች ውስጥ እየኖሩ እንዲቀጥሉ እንደ መብት መመስረቻ በመቁጠር አቤቱታ ማቅረባቸው ተገቢነት የለውም፤ አመልካቾች አሁን በእጃቸው የሚገኘው ቤት ውስጥ የመኖር መብታቸው የሚጠናቀቀው አዲሱ ምክር ቤት ሥራ ከሚጀምርበት ከአንድ ወር በፊት በመሆኑ ቤት የማግኘት መብታችን የማይቋረጥ ነው በማለት የሚያቀርቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፤ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ብይን እና ትዕዛዝ ሊጸና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካቾችም 2ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ላይ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://chilot.me

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በማስቀረቢያ ነጥቡ ሳይወሰን አጠቃላይ የግራ ቀኙን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከክርክሩ አጀማመር መረዳት እንደሚቻለው አመልካቾች ክስ ያቀረቡት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል በመሆናችን ምክንያት ለመኖሪያነት ተሰጥቶን የነበረውን ቤት የውክልና ጊዜያችሁ አልቋል በሚል ምክንያት እንድንለቅ እንቅስቃሴ መጀመሩ የሁከት ተግባር በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ ከኃላፊነቱ ለተነሱ የመንግስት ባለስልጣናት እና ኃለፊዎች ማግኘት ስለሚገባቸው ጥቅማጥቅም በሚደነግገው አዋጅ ቁጥር 653/2001 እና 1003/2009 መሰረት የሚገባን ጥቅማጥቅም እስኪሟላልን ድረስ በቤቱ ውስጥ እንድንኖር ሊወሰን ይገባል በሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ክስ የቀረበበትን ቤት በተመለከተ ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ተከራይቼ በየዙሩ በህዝብ እንደራሴነት ለሚመረጡት ተወካዮች መኖሪያነት በመስጠት የውክልና ጊዜያቸው ሲያበቃም እየተቀበልኩ አዲስ ለሚመረጡት ሳስተላልፍ የቆየሁ ቤት ነው፤ ጥቅማጥቅም የማሟላት ኃላፊነት ያለብኝም በስራ ላይ ያሉትን የህዝብ እንደራሴዎችን በሚመለከት እንጂ የውክልና ጊዜያወቸውን ያጠናቀቁትን አይደለም፤ የውክልና ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ የህዝብ እንደራሴዎችን ጉዳይ በተመለከተ በህግ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅማጥቅም የማሟላት ኃላፊነቱ የአስፈፃሚው የመንግስት አካል እንጂ የጽ/ቤቱ ባለመሆኑ አመልካቾች በጽ/ቤቱ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችላቸው መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡

እንግዲህ የፍትሓ ብሔር ሙግት የሚመራው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ነው፡፡ አሁን ስራ ላይ ያለው የ1958ቱ የፍትሓ ብሔርሥነ ሥርዓት ህግ በሁለተኛው መፅሓፍ ስለ ጠቅላላ ደንቦች በሚደነግገው ምዕራፍ አንድ ቁጥር 33 ስር በአንድ የፍትሓ ብሔር ክርክር ማናቸውም ሰው ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ላይ ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ክስ ማቅረብ የማይፈቀድለት መሆኑን፤ እንዲሁም ከተከሳሽ ላይ የሚጠይቀውን ጥቅም ወይም መብት በማረጋገጥ አቤቱታ ካላቀረበ በቀር በማናቸውም ሰው ላይ ክስ ሊያቀርብ የማይችል ስለመሆኑ ተደንግጓል፡፡

በሌላ በኩል በይዞታዬ ላይ ሁከት ተፈጥሮብኛል የሚል ማንኛውም ሰው ክስ ባቀረበበት ንብረት ላይ በህግ ጥበቃ የሚደረግለት የይዞታ መብት ያለው መሆኑን እና በዚሁ ህጋዊ ይዞታው ላይ በተከሰሰው ሰው/አካል ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሁከት የተፈጠረበት ስለመሆኑ ማሳየት ያለበት እንደሆነ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149(1) ይደነግጋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አሁን በቀረበው ጉዳይ አመልካቾች በ1ኛ ተጠሪ ላይ ክስ ከማቅረባቸው ውጭ ከዚሁ ተጠሪ ላይ የሚጠይቁ መብት ምን እንደሆነ እና ተጠሪ ለእነርሱ የዳኘነት ጥያቄ ተጠያቂ የሚሆንበትን ምክንያት የገለፁት ነገር የለም፡፡ አመልካቾች በዚህ መልኩ ከ1ኛ ተጠሪ የሚጠይቁት መብት ወይም ጥቅም ምን እንደሆነ አልያም በዚሁ ተጠሪ የተፈፀመው ህገ ወጥ ተግባር ምን እንደሆነ ለይተው ባላመለከቱበት 1ኛ ተጠሪ በተከሳሽነት የሚቀርብበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች 1ኛ ተጠሪን ለማክሰስ የሚያስችላቸው መብት እና ጥቅም የላቸውም በማለት ክሱን ውድቅ ማድረጋቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 33/2/ ድንጋጌን መንፈስ የተከተለ ከሚባል በቀር የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በተያያዘ አመልካቾች ለክሱ ምክንያት የሆኑትን ቤቶች የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ከመሆናቸው ጋር ታያይዞ የተሰጣቸው ስለመሆኑ የቀረበው ክስ በራሱ ያሳያል፡፡ በዚህ መልኩ ቤት የተሰጣቸው የምክርቤቱ አባላት የውክልና ጊዜያቸው እንደተጠናቀቀ አድስ ተመራጮች ስራ ከመጀመራቸው አንደ ወር ቀደም ብሎ ቤቱን ለጽ/ቤቱ የማስረከብ ግዴታ ያለባቸው ለመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ለዚሁ ጉዳይ አግባብነት ያለውን መመሪያ ጠቅሶ መልስ ሰጥቷል፡፡

የኢ.ፌ.ድ.ሪ. የሕዝብ ተወካዩች ምክር አባላትን ጥቅማጥቅም ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 40/2012 አንቀጽ 11/10/ የውክልና ጊዜውን የጨረሰ እና ድጋሚ ያልተመረጠ አባል ንዑስ አንቀት ሀ፦ “ አዲሱ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ከሚጀመርበት እለት ከአንድ ወር በፊት እስከ ነሐሴ 30 ቤቱን ማስረከብ አለበት ፡፡” በሚል ይደነግጋል፡፡

ከዚህ መመሪያ ድንጋጌ መገንዘብ የምንችለው ውክልናቸውን የጨረሱ እና ምክር ቤቱ በተከራየው ቤት ውስጥ ሲኖሩ የቆዩ አባላት የህዝብ ውክልና ይዘው አዲስ በሚመጡ አባላት የሚተኩ በመሆኑ በድጋሚ እስካልተመረጡ ድረስ የአዲሱ ምክር ቤት ሥራ ከመጀመሩ ከነሐሴ 30 በፊት ቤቱን ለቀው ለአዲስ ተመራጭ አባላት ማስረከብ ያለባቸው መሆኑን ነው፡፡

አመልካቾች በመመሪያው አንገደድም በሚል ያቀረቡት ተቃራኒ ክርክር የለም፡፡ አመልካቾች ክስ የቀረበበትን ቤት የውክልና ጊዜያቸው እንደተጠናቀቀ ለ2ኛ ተጠሪ የማስረከብ ከህግ የመነጨ ግዴታ ካለባቸው እና የእንደራሴነት ጊዜያቸው መጠናቀቁ ካላከራከረ አመልካቾች በቤቱ ላይ በህግ ጥበቃ የሚደረግለት የይዞታ መብት የላቸውም ማለት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካቾች ለክሱ ምክንያት የሆነውን ቤት አስምልክቶ በ2ኛ ተጠሪ ላይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ መብት የሌላቸው በመሆኑ ክሱ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ ነው፡፡

https://chilot.me

አመልካቾች ከቀድሞ ሀገራዊ ኃለፊነታቸው ጋር በተያያዘ በህግ ማግኘት ሲገባቸው ያልተሟላላቸው ጥቅማ ጥቅም ካለ በህግ አግባብ ኃላፊነት ያለበትን አካል አግባብ ባለው መንገድ ከሚጠይቁ በቀር ጥቅማ ጥቅሙ እስኪሟላልን ድረስ የያዝነውን ቤት አንለቅም የሚሉበት ከህግ አልያም ከውል የመነጨ መብት የላቸውም፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ወሳኔ በአብላጫ ድምጽ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/282281 ላይ ጥር 23/20014 ዓ.ም በዋለው ችሎት በስር ፍርድ ቤት የተሰጥውን ብይን በማፅናት የሰጠው የመጨረሻ ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንተዋል፡፡

2. ይህ ውሳኔ አመልካቾች ከቀድሞ ኃላፊነታቸው ጋር በተያያዘ በህጉ አግባብ ማግኘት የሚገባቸውን መብት እና ጥቅማጥቅም ስልጣን ላለው አካል አቅርበው ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይደለም፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

አ/ኃ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

https://chilot.me



# የሀሳብ ልዩነት

እኔ ስሜ በተራ ቁጥር 3 የተመለከተው የችሎቱ ዳኛ አብላጫው ድምፅ 1ኛ ተጠሪን አስመልክቶ በደረሰበት ድምዳሜ የምስማማ ቢሆንም ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በተያያዘ አመልካቾች የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ከህግም ሆነ ከውል የመነጨ መብት የላቸውም በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ብይን በማፅናት በሰጠው ውሳኔ ያልተስማማሁ በመሆኑ ለልዩነት መነሻ የሆኑኝን ምክንያቶች እንደሚከተለው አስፍሬያለሁ፡፡

በመሰረቱ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ለጉዳዩ አግባብነት ባለው 2ኛ ተጠሪ ላይ ክሱን ያቀረቡት በቅድሚያ በአከራካሪዎች ቤቶች ላይ በተከራይነት የመቀጠል ከህግ የመነጨ መብት ያላቸው መሆኑን በማሳየት እነዚህ መብቶች ቢኖሯቸውም 2ኛ አመልካች ቤቶቹን እንዲለቁ በመጠየቅ ሁከት እየፈጠረባቸው መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡አመልካቾች ከቤቱ ለቀን ልንወጣ አይገባም በማለት የሁከት ይወገድልን ክስ ያቀረቡ በመሆኑ ይህንን ክስ ለማቅረብ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33(2) መሰረት ክሱን ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም ያላቸው መሆኑን ለማሳየት በፍ/ብ/ህ/ቁ.1140 አግባብ በአከራካሪዎቹ ቤቶች ላይ በእውነት የሚያዙበት መብት ያላቸው ለመሆኑ ማሳያ ማቅረባቸው በቂ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ክሱ በስር ፍርድ ቤቶች በመቃወሚያ ደረጃ ውድቅ የተደረገ ከመሆኑ አንፃር በመቃወሚያ ደረጃ ሊታይና ሊመረመር የሚገባው አመልካቾች በቤቶቹ ላይ የይዞታ መብት ያላቸው ለመሆኑ ማሳያ ማቅረብ አለማቅረባቸው ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡

አሁን በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች ቤቶቹን ይዘው እየተገለገሉበት ለመሆኑ፤2ኛ ተጠሪም ቤቶቹን ለቀው እንዲያስረክቡት መጠየቁ በግራ ቀኙ ያልተካደ ነጥብ ሆኖ እያለ ይህ ደግሞ አመልካቾች የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል በቂ ማሳያ ማቅረባቸውን በግልፅ እያሳየ የስር ፍርድ ቤቶች ለፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.33(2) ጥብቅ መስፈርት በማስቀመጥ አመልካቾች ክርክራቸውን ክርክሩ በመቃወሚያ ደረጃ እያለ ማረጋገጥ ያለባቸው መሆኑን በማመልከት የመክሰስ መብት የላቸውም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው የስነ ስርዓት ህጉን መሰረት ያላደረገ